https://chilot.me

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፮
አዲስ አበባ ታህሳስ ፫ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

23rd Year, No. 6
ADDIS ABABA, 12th December, 2016

## ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፺፬/፪ሺ፱ ዓ.ም

የሥራ ፈቃድ፣ የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ ፈቃድ እና የሥራ ውል ማፅደቂያ የአገልግሎት ዋጋ ክፍያዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ…………………ገጽ ፱ሺ፬፻፴፪
ሰንጠረዥ……………………………………….....ገጽ ፱ሺ፬፻፴፬

## CONTENT

Council of Ministers Regulation No.394 /2016

Rate of Fee for Work Permit, Private Employment Agency License and Approval of Contract of Employment Council of Ministers Regulation……………………………………page 9432
Schedule……………………………………. page 9434

**የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፺፬/፪ሺ፱**

**<u>የሥራ ፈቃድ፣ የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ ፈቃድ እና የሥራ ውል ማፅደቂያ የአገልግሎት ዋጋ ክፍያዎችን ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>**

**COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No.394/2016**

**<u>COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE DETERMINATION OF FEES FOR WORK PERMIT, PRIVATE EMPLOYMENT AGENCY LICENSE AND APPROVAL OF CONTRACT OF EMPLOYMENT</u>**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፮/፪ሺ፯ አንቀጽ ፭፣ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር ፫፻፸፯/፲፱፻፺፮ አንቀጽ ፩፻፸፬(፬)፣ በኢትዮጵያ ፌደራል መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፮፻፵፰/፪ሺ፩ አንቀጽ ፲፯(፩) እና በኢትዮጵያ የውጭ አገር ሥራ ስምሪት አዋጅ ቁጥር ፱፻፳፫/፪ሺ፰ አንቀጽ ፸፭(፩) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 916/2015, Article 174(4) of the Labour Proclamation No. 377/2003, Article 17(1) of the Federal Government of Ethiopia Financial Administration Proclamation No.648/2009 and Article 75(1) of the Ethiopia's Overseas Employment Proclamation No. 923/2016.

### ፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ "የሥራ ፈቃድ፣ የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ ፈቃድ እና የሥራ ውል ማፅደቂያ የአገልግሎት ዋጋ ክፍያዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፺፬/፪ሺ፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 1. <u>Short Title</u>

This Regulation may be cited as the "Rate of Fee for Work Permit, Private Employment Agency License and Approval of Contract of Employment Council of Ministers Regulation No.394/2016".

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

https://chilot.me



**፪. ትርጓሜ**

በዚህ ደንብ ውስጥ:-

፩/ "የሥራ ፈቃድ" ማለት አንድ የውጭ አገር ዜጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ተቀጥሮ ለመሥራት እንዲችል በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር ፫፻፸፯/፲፱፺፮ አንቀጽ ፩፻፸፬(፬) መሠረት የሚሰጥ ፈቃድ ነው፤

፪/ "አዋጅ" ማለት የኢትዮጵያ የውጭ አገር ሥራ ስምሪት አዋጅ ቁጥር ፱፻፳፫/፪ሺ፰ ነው፤

፫/ በአዋጁ የተሰጡ ትርጓሜዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

**፫. ስለ አገልግሎት ክፍያ**

የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር ፫፻፸፯/፲፱፺፮ አንቀጽ ፩፻፸፬(፬)፣ በኢትዮጵያ የውጭ አገር ሥራ ስምሪት አዋጅ ቁጥር ፱፻፳፫/፪ሺ፰ አንቀጽ ፲፩፣፳፭ እና ፴፫ (፫) በተደነገገው መሠረት ለሚሰጠው አገልግሎት ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ በተመለከተው ተመን መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ያስከፍላል፡፡

**፬. የተሻረ ሕግ**

የሥራ ፈቃድ እና የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ ፈቃድ ክፍያዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፹፪/፪ሺ፭ በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

**፭. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ታህሳስ ፫ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**2. Definition**

In this Regulation:

1/ “work permit” means a permit issued to a foreign national pursuant to Article 174(4) of the Labour Proclamation No.337/2003 to work in Ethiopia as an employee;

2/ “Proclamation” means the Ethiopia’s Overseas Employment Proclamation No. 923/2016;

3/ definitions provided under the Proclamation shall be applicable.

**3. Service Fees**

Service fees shall be payable for services rendered by the Ministry of Labour and Social Affairs in Accordance with Article 174(4) of the Labour Proclamation No. 377/2003 and Articles 11, 25 and 33(3) of the Ethiopia’s Overseas Employment Proclamation No.923/2016 at the rate prescribed in the schedule attached herewith.

**4. Repeal Law**

The Work Permit and Private Employment Agency License Fees Council of Ministers Regulation No. 282/2013 is hereby repealed.

**5. Effective Date**

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 12th day of December 2016.**

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

https://chilot.me



## የአገልግሎት ክፍያ ሠንጠረዥ

| ተ.ቁ | የአገልግሎት ዓይነት | የክፍያ መጠን በብር | | |
|---|---|---|---|---|
| | | አዲስ ፈቃድ | ዕድሳት | ምትክ ፈቃድ |
| 1 | የውጭ አገር ዜጎች የሥራ ፈቃድ | 2000 | 1500 | 1200 |
| 2 | የውጭ አገር የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ የሥራ ፈቃድ | 3300 | 3000 | 2700 |
| 3 | የአገር ውስጥ የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ የሥራ ፈቃድ | 650 | 550 | 450 |
| 4 | የሥራ ውል ማጽደቂያ | 500 | | |



## SCHEDULE OF FEES

| No. | Types of Services | Amount of Fee (Birr) | | |
|---|---|---|---|---|
| | | For New License | For Renewal of License | For Replacement of License |
| 1. | Issuance of Work Permit for Foreigners | 2000 | 1500 | 1200 |
| 2. | Issuance of Overseas Private Employment Agency License | 3300 | 3000 | 2700 |
| 3. | Issuance of Local Private Employment Agency License | 650 | 550 | 450 |
| 4. | Approval of Contract of Employment | 500 | | |